# የክህሎት መመዘኛ ፈተና አጠቃላይ መመሪያዎች

የክህሎት መመዘኛ ፈተናዎን ለመውሰድ እየጠበቁ ሳሉ እነዚህን መመሪያዎች ያንብቡ።
ይህ ካርድ መመዘኛ ፈተናዎን ለሚሰጥ ገምጋሚ የግድ መመለስ አለበት።

**ወደ የፈተና ክፍል ሲጠሩ፣ ገምጋሚው የሚከተሉትን ያደርጋል፦**

- መታወቂያዎን ለማየት ይጠይቃል።
- ለፈተናው የሚያስፈልጉትን አቅርቦቶች እና መሳሪያዎች ማየት እንዲችሉ በክፍሉ ዙሪያ ያሳዩዎታል።

**ለክህሎት መመዘኛ ፈተና** በደንበኛ እንክብካቤ ድርጊት ሊያከናውኗቸው የሚችሏቸውን ሶስት ክህሎቶችን ይፈፅማሉ። እነዚህን ክህሎቶች በሚያከናውኑበት ጊዜ፣ አንድ ገምጋሚ የእርስዎን የአፈጻጸም ብቃት እየተመለከተ ይመዘግባል። ክህሎቶቹ የሚከናወኑት በአንድ የደንበኛውን ሚና በሚጫወት እጩ ላይ ወይም በአሻንጉሊት ላይ ነው። ለተዋናዩ ወይም ለአሻንጉሊቱ፣ እሱ/ሷ ልክ እውነተኛ ደንበኛ እንደሆኑ አድርገው ማነጋገር አለብዎት።

**የመመዘኛ ፈተናዎን ከመውሰድዎ በፊት፣ ገምጋሚው የሚከተሉትን ያደርጋል፦**

- ለእያንዳንዱ ክህሎት መመሪያዎችን የያዘ ለመመዘኛ ፈተና ሊያከናውኗቸው የሚገቡ የክህሎቶች ዝርዝርን የያዘ ካርድ ይሰጥዎታል።
- ለእያንዳንዱ ክህሎት መመሪያዎችን ያነብልዎታል። (እንግሊዝኛ ያልሆነ የመመዘኛ ፈተና የሚወስዱ ከሆነ አስተርጓሚ ይረዳዎታል።)
- የመመዘኛ ፈተናዎን መቼ እንደሚወስዱ እና መቼ ለሌላ ተወዳዳሪ መመዘኛ ፈተና የደንበኛን ሚና እንደሚጫወቱ ይነግርዎታል።

**ለክህሎቶች የመመዘኛ ፈተና፣ ደንበኛው፦**

- በአእምሮ ንቁ እና ተባባሪ እንደ ሆነ ይታሰባል።
- በተወሰኑ ክህሎቶች ወቅት አካላዊ ገደቦች ሊኖሩት ይችላል።

**ደንበኛው በአንድ ሰው ተወክሎ ሲጫወት** (በአሻንጉሊት ካልሆነ)፣ **ሰውየው፦**

- እንዲናገር የሚፈቀድለት ጥያቄዎችዎን ለመመለስ ብቻ ነው።
- ሊንቀሳቀስ እና በእንቅስቃሴ ላይ ሊረዳዎት ይችላል።
- ለመንቀሳቀስ ሲጠየቅ ብቻ ይንቀሳቀሳል።

**የደንበኛን ሚና ሲጫወቱ እርስዎ፦**

- ንቁ እና ተባባሪ እና መንቀሳቀስ የሚችሉ እና አቅጣጫዎች መከተል የሚችሉ ደንበኛ ነዎት።
- እጩው እንዲንቀሳቀሱ ሲጠይቁዎት ብቻ ነው መንቀሳቀስ ያለብዎት።
- በእጩው የተጠየቀውን ጥያቄ ለመመለስ ብቻ መናገር አለብዎት።
- እንደ ደንበኛ ያለዎትን ሚና በተመለከተ ከገምጋሚው ልዩ መመሪያዎችን ሊቀበሉ ይችላሉ።
- ሌላውን እጩ በምንም መልኩ ሊረዱ አይችሉም። ይህም ቃላትን፣ ምልክቶችን ወይም የፊት መግለጫዎችን በመጠቀም ፍንጭ መስጠትን ይጨምራል። ይህ ዓይነቱ ባህሪ እንደ ማጭበርበር ይቆጠራል እና ሁለቱም እጩዎች የምርመራ ውጤቶችን ሳይቀበሉ ከፈተና እንዲባረሩ ያደርጋል። ክስተቶች ለWashington Department of Health ሪፖርት ይደረጋሉ።

**የክህሎት መመዘኛ ፈተናዎን በሚወስዱበት ጊዜ ማስታወስ ያለብዎት የሚከተሉትን ጥቂት ነጥቦች ነው፦**

- ክህሎቶቹን በእውነቱ ማከናወን አለብዎት።
- ክህሎቶቹን ገምጋሚው በሚሰጥዎ የመመሪያ ካርድ ላይ በቅደም ተከተል በተዘረዘሩበት አግባብ ማከናወን አለብዎት። በመመዘኛ ፈተናዎ ወቅት በማንኛውም ጊዜ የመመሪያ ካርዱን እንደገና ማንበብ ይችላሉ።
- ለእያንዳንዱ ክህሎት መመሪያዎቹን በጥንቃቄ ያንብቡ። ለዚህ የመመዘኛ ፈተና፣ ለሶስቱም ክህሎቶች ከአንድ ደንበኛ ጋር እየሰሩ እንደሆነ ያስመስላሉ፣ ምንም እንኳን አንድ ተዋናይ ደንበኛው ለአንድ ክህሎት ሊጫወት እና አሻንጉሊት ደግሞ ለሌላ ክህሎት እንደ ደንበኛ ጥቅም ላይ ሊውል ቢችልም። በአንዳንድ ክህሎቶች፣ መመሪያዎቹ ስለ ደንበኛ ችሎታዎች ወይም ገደቦች የተለየ መረጃ ይሰጣሉ። ለምሳሌ፣ በአለባበስ ክህሎት ተዋናዩ ደካማ ክንድ ያለው ደንበኛን ይወክላል። ያ ልዩ የአካል ገደብ የሚመለከተው በአለባበስ ክህሎት ላይ ብቻ ነው። ስለ ደካማ ክንድ የተሰጡ ልዩ መመሪያዎች፣ በሌሎቹ ሁለት ክህሎቶች ላይ ለደንበኛው አይተገበሩም።

**ከኋላ ማንበብ ለመቀጠል ካርዱን ይገልብጡ➔**


Copyright © 2010 Prometric Inc., a Delaware corporation. All rights reserved. 

- ክህሎቶችን ለማከናወን የሚያስፈልጉት አቅርቦቶች እና መሳሪያዎች በየመመዘኛ ፈተና ክፍል ውስጥ ይገኛሉ። ማግኘት ያልቻሉት ነገር ካለ ገምጋሚውን ይጠይቁ።
- አንድ ክህሎት ማከናወን ሲጨርሱ "ጨርሻለሁ" ይበሉ።
- በክህሎት ፈተና ወቅት ስህተት ሰርቻለሁ ብለው ካሰቡ፣ እርማት ለማድረግ ወደ ኋላ እንደሚመለሱ ለገምጋሚው ማሳወቅ አለብዎት። እርስዎ እየሰሩት ባለው ክህሎት ላይ ብቻ እርማቶችን ማድረግ ይችላሉ። አንድ ጊዜ አንድን ክህሎት ማከናወን እንደጨረሱ ከተናገሩ፣ ወደዚያ ክህሎት ላይመለሱ ይችላሉ።
- ገምጋሚው የመመሪያ ካርዱን ሲሰጥዎ፣ መመዘኛ ፈተናውን ለመውሰድ ስንት ደቂቃ እንዳልዎት ይነገርዎታል። የጊዜ መጠን በክህሎቶች ላይ መሰረት ያደረገ ነው። የመጀመሪያውን ክህሎት በጀመሩበትን ጊዜ ገምጋሚው መቁጠር ይጀምራል፣ እና ፈተናዎ ከማብቃቱ በፊት አምስት ደቂቃ ጊዜ ሲቀር ይነገርዎታል።
- የመጨረሻውን ክህሎት ሲጨርሱ፣ ለደንበኛው ለቀኑ እንክብካቤውን እንደጨረሱ አድርገው ይያዙት።
- በመመዘኛ ፈተናው ወቅት ገምጋሚው ከባድ የደህንነት ስጋት ካለው፣ የክህሎት ምርመራው ይቆማል፣ እና ያ ክህሎት ያበቃል።
- የግዛት መመዘኛ ፈተና እየወሰዱ ነው። ገምጋሚው እርስዎን እንዲረዳዎ ወይም እንዲያስተምርዎ ወይም ስለ አፈጻጸምዎ ከእርስዎ ጋር እንዲወያይ አይፈቀድለትም።

**የመመዘኛ ፈተናዎ ሲያልቅ፣ ገምጋሚው የሚከተሉትን ያደርጋል፦**
- ከክህሎት አፈጻጸምዎ መረጃን ወደ ኮምፒውተሩ ያስገባል፣ ይህም የመመዘኛ ፈተናውን ነጥብ ይመዘግባል።
- የውጤት ሪፖርትዎን ስለማግኘት መረጃ የያዘውን የማጠናቀቂያ ደብዳቤ ለመፈለግ ኢሜልዎን እንዲከታተሉ ትዕዛዝ ይደርስዎታል።

**ለዚህ የመመዘኛ ፈተና የሚመለከቱ ሌሎች አጠቃላይ ህጎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**
- በመመዘኛ ፈተና ወቅት የመቅጃ መሳሪያዎች፣ ሞባይል ስልኮች፣ ድምጽ የሚያስተላልፉ ኤሌትሮኒክ እቃዎች፣ ግላዊ ዲጂታል ረዳት (Personal Digital Assistant, PDA) ወይም ካሜራዎች መጥፋት እና መቀመጥ አለባቸው።
- እርስዎ የያዙት ማንኛውም የግል እቃዎች በመመዘኛ ፈተና ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው እና በፈተናዎ ጊዜ ወደ ንብረቶችዎ እንዲደርሱ አይፈቀድልዎትም።
- ይህ የዝግ መጽሐፍ ፈተና ነው። በመመዘኛ ፈተና ወቅት ማንኛውንም ማስታወሻዎች፣ መጽሐፎች ወይም የእጩ ማስታወሻ ነጥቦችን መጠቀም ወይም ማየት አይፈቀድልዎትም።
- በዚህ የመመዘኛ ፈተና ወቅት ምንም የተፈቀዱ እረፍቶች የሉም።
- የእንግሊዘኛ ያልሆነ የክህሎት መመዘኛ ፈተና ለመውሰድ ካልተመዘገቡ በቀር፣ መመዘኛ ፈተናዎን እየወሰዱም ሆነ ደንበኛን እያነጋገሩ ሳለ በመመዘኛ ፈተና ወቅት በእንግሊዝኛ ብቻ መናገር ይጠበቅብዎታል።
- ባህሪዎ ጸያፍ ከሆነ ወይም የሚረብሽ ከሆነ፣ የመመዘኛ ፈተናዎ ይቋረጣል እና ከፈተናው ይባረራሉ። ገምጋሚው ሌላ ሰው እያስመሰሉ ነው ብሎ ካመነ ወይም በማጭበርበር ከተጠረጠሩ ከፈተናው ይባረራሉ።
- ገምጋሚው በመመዘኛ ፈተና ክፍል ውስጥ ማብራርያ ከሰጠዎ በኋላ ስለእነዚህ መመሪያዎች ጥያቄዎችን የመጠየቅ እድል ይኖርዎታል።


Copyright © 2010 Prometric Inc., a Delaware corporation. All rights reserved.